# በቤት-ውስጥ የደም ግፊት መቆጣጠሪያ መሳሪያዎን ለመምረጥ




የደም ግፊትዎን በቤትዎ ውስጥ እንዳሉ መለካትና መቻል፣ እርስዎ እና የእንክብካቤ ቡድንዎ የደም ግፊትዎን በተሻለ ሁኔታ መከታተል እና መቆጣጠር እንዲትችሉ ይረዳችኋል። ትክክለኛውን የደም ግፊት መለኪያዎን እንዴት መምረጥ እንዳለብዎት የሚጠቅሙዎት ጥቂት ምክሮች እነሁልዎት፡

## እኛ የምንመክረው፡

1. አንድ ቁልፍ በመንካት የደም ግፊትዎን በራስ-ሰር (አውቶማቲካሊ) የሚያነብ በላይኛው ክንድ ላይ የሚደረግ የግፊት መለኪያ።
2. የደም ግፊት መለኪያው ማሰሪያ (ካፍ) በበርከታ የተለያዩ የልክ መጠኖች ይገኛሉ። ትክክለኛውን የደም ግፊት ንባብ ማግኘትዎን ለማረጋገጥ፣ በላይኛው ክንድዎ ላይ የሚታሰረው (የሚጠመጠመው) ካፍ ለርስዎ የሚስማማ ትክክለኛ መጠን መሆኑን ያረጋግጡ።
3. በጣም ትክክለኛ የሆነ ንባብ ማግኘትዎን ለማረጋገጥ፣ መሳሪያዎ በባለሙያ ተረጋግጦ የተፈቀደ መሆኑን ያረጋግጡ። በአሜሪካ የህክምና ማህበር ማረጋገጫ ተሰጥቷቸው ለተዘመኑ መሳሪያዎች ዝርዝር፣ እባክዎ ይህን አገናኝ www.validatebp.org ይጎብኙ።
4. አንዴ የደም ግፊት መቆጣጠሪያዎን ካገኙ በኋላ፣ በቢሮ ውስጥ ካሉ የግፊትዎ ንባቦች ጋር ለማነፃፀር ወደ አገልግሎት ሰጪዎ ቢሮ ያቅርቡ።

## የደም ግፊት (BP) መልኪያ/መከታተያዎን ስለማግኘት፡

- የጤና አጠባበቅ አገልግሎት አቅራቢዎ ካዘዘ፣ ለደም ግፊት መለኪያው ካፍ (ማሰሪያ) የሚሆን ወጪን የጤና መድህን/ኢንሹራንስ አገልግሎትዎ በከፊል ወይም በሙሉ ሊከፍል ይችላል።
  - የጤና ኢንሹራንስዎ መሳሪያውን ለመግዛት የሚያስፈልገውን ወጪ የሚሸፍን እንደሆነ የCHA ማዕከላዊ የድጋሜ መሙላት ፋርማሲ ሊያረጋግጥ ይችላል።
  - እነዚህን በማንኛውም ፋርማሲ ወይም የችርቻሮ መደብር (ማለትም፣ ከታርጌት፣ ከዎልማርት፣ ከአማዞን ወዘተ) ማግኘት ይችላሉ።
- ኢሹራንሱ ለደም ግፊት መከታተያው መግዣ የማይከፍል ከሆነ፡
  - የእፎታ መፈናፈኛ ያላቸው (ፍሌክሲብል) ወጪዎች ወይም የጤና ቁጠባ ሂሳቦች የደም ግፊት መቆጣጠሪያ መሳሪያ መግዣውን ለመክፈል ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ።
  - ለደም ግፊት መቆጣጠሪያዎ ቅናሾችን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ የCHA የእንክብካቤ ቡድንዎን ይጠይቁ፣ ወይም የብድር ፕሮግራማችንን ይጠቀሙ።

CHA Cambridge Health Alliance

CARE TO THE PEOPLE

### በጣም የሚታወቁ እና የተለመዱ ለሆኑት የደም ግፊት መለኪያዎች/መቆጣጠሪያዎች የበለጠ ለማወቅ፣ ከዚህ በታች የሰፈረውን ሰንጠረዥ ይጠቀሙ፡

| ስም* | Omron 3 Series | Welch Allyn 1700 series | Omron 7 Series |
|---|---|---|---|
| **ምስል/ስዕል** |  |  |  |
| **ወጪ/ዋጋ፡** | $35 | $100 | $63 |
| **ማህደረ-ትውስታ፡ (ሜሞሪ)** | 14 ንባቦች፣ መተግበሪያ የሌለው | 99 ንባቦች፣ ንባቦቹን መከታተል፣ እና በኢሜይል መላክ | 90 ንባቦች፣ ንባቦቹን መከታተል፣ እና በኢሜይል መላክ |
| **ገጽታዎቹ / ባህሪያቱ** | የላይኛው ክንድ ክፍል ላይ የሚታሰር ካፍ 9''-13'' | በመደበኛ እና በበጣም ትልቅ (XL) የካፍ መጠን ይገኛል | ሞልዲድ ካፍ 9''-13,'' ለመጠቀም በጣም ቀላል |

**የአንዳንድ መደብሮች ብራንዶች ወቅታዊነታቸው የተረጋገጠላቸው ሆነው እንዲሁም በዝቅተኛ ዋጋ ሊገኙ ይችላሉ።*

**የበለጠ ለማወቅ የQR ኮዱን ስካን ያድርጉ**

CHA Cambridge Health Alliance

GR25_138